# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 58 ሰኔ 18 2001 ዓ.ም


.... «ኤፈርት-መር ካፒታሊዝም» የተሰኘው የወያኔ ኢኮኖሚ መሠረቱ ሸቀጦችን ማምረት ወይም አገልግሎቶችን ማቅረብ ሳይሆን ከለጋሽ አገሮች የሚገኝ እርዳታን መምጠጥ ነው፡፡ የእርዳታ ፍሰት የወያኔ የሕይወት እስትንፋስ ነው፡፡ ስለሆነም በችግርኛው ስም የሚመጣው እርዳታ ወደ ወያኔ ቋቶች ያለማቋረጥ መፍሰሱን ማረጋገጥ የሹመኞቹ የሙሉ ጊዜ ሥራ ነው፡፡ ወያኔ ምን ያህል በእርዳታ ሱስ የሰከረ ስለመሆኑ በያዝነው ሰኔ ወር ብቻ እንኳን ካስተዋልናቸው ክስተቶች ውስጥ ሶስቱን ብቻ ለአብነት እናነሳለን **የግንቦት 7 ርእሰ አንድቀጽ**

## በመከላከያ ሠራዊቱ ውስጥ ያለው የአዛዥነት ቦታዎች በትግራይ ተወላጆች መያዙ ከፍተኛ ቁጣን ቀሰቀሰ

በመከላከያ ሠራዊቱ ውስጥ ያለው የአዛዥነት ቦታዎች በትግራይ ተወላጆች የበላይነት መያዙን የግንቦት 7 ንቅናቄ ለህዝብ ይፋ ማድረጉን ተከትሎ በሠራዊቱና በፖሊስ አባላቱ ውስጥ ከፍተኛ ቁጣን የቀሰቀሰ መሆኑ ተሰማ። የግንቦት 7 ድምፅ ባለፈው ግንቦት 21 ቀን፡- " **በመከላለከያ ሠራዊት ውስጥ ባሉ ቁልፍ የአዛዥነት ቦታዎች ላይ የሚገኙ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች የብሔረሰብ ተዋፅኦን"** በሚመለከት ይፋ ያደረገው ዘገባ፤ በተለያዩ የሠራዊቱ ክፍሎች ዘንድ ቁጣ መቀስቀሱ፤ በፌዴራል ፖሊስ አባላት ዘንድ ደግሞ ንዴት፣ እልክና ቁጭት መጫሩ ታወቀ።

በሠራዊቱ ውስጥ የሚገኙት የንቅናቄው ምንጮች ያደረሱን መረጃ እንደሚያመለክተው፣ በአገሪቱ ካሉት 61 ቁልፍ የመከላከያ ሥልጣኖች መካከል በሚያሳፍርና "ጉድ" በሚያሰኝ ሁኔታ 57ቱ ለትግሬ ተወላጆች መሰጠታቸውን የተነተነው የግንቦት 7 ዘገባ ይፋ መሆኑን ተከትሎ፤ በተለይ በብሔረ-አማራ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) እና በኦሮሞ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) ክፍለ-ጦሮች ውስጥ ከፍተኛ ጥያቄና ቁጣ ማስነሳቱ ታውቋል።

በዝቅተኛ ማዕረግ የሚገኙና በተራ ተዋጊነት እያገለገሉ ያሉ የአማራና የኦሮሞ ተወላጅ የሠራዊቱ አባላት፣ "ይህን ዓይነቱን የለየለትና ዐይን ያወጣ የዘረኝነት ሹመት እስከዛሬ ያልነገራችሁን ለምንድነው? የሚመለከቱንን መረጃዎች ለምን ትደብቁናላችሁ? ፍትህዊ የብሔረሰብ ተዋፅኦ ማለት ይሄ ነወይ?" የሚሉ የቁጭት ጥያቄዎችን ለአለቆቻቸው በስፋት ማንሳታቸውን የገለፁት ምንጮቻችን፤ ነገሩን የሚያውቁት አለቆቻቸው ሳይቀሩ እንደ አዲስ ግራ ከመጋባት ውጪ የሚናገሩት ስለሌላቸው ጉዳዩ በብዙዎቹ የሠራዊቱ አባላት ዘንድ ሊበርድ ያልቻለ አጀንዳ ሆኗል ብለዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በመፈራረስ ላይ ያለው የዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ሰራዊት አባለት ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በመሸሽ ላይ ናቸው

በመፈራረስ ላይ ያለው የዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ሰራዊት አባለት ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በመሸሽ ላይ ናቸው። በመከላከያ ሚኒስትር የሲሙሌተር መምሪያ ሀላፊ እና ዋና ኤክስፐርት የነበረው ወታደራዊ መሀንዲስ ዳዊት ሀይሉ ደስታ ለስልጠና ከተለካበት ቼክ ሪፑብልክ አምልጦ በአንድ የአውሮፓ ሀገር ጥገኝነት መጠየቁን ኢትዮ ፍሪደም የተባለ ድረ ገጽ ዘገቧል። ኢንጅነር ዳዊት የመከላከያ ኢንጅነሮች መስሪያ ቤቱን ላልተወሰነ ጊዜ ማገልገል አለባቸው የሚለውን አስገዳጅ የወያኔ ህግ በመቃወም ለእስር ተዳርጎ እንደነበረ የገለጸው ዘገባ፤ በወያኔው የመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ከፍተኛ አፈና እንዳለ አትቷል።

በመከላከያ ሰራዊቱ ውስጥ ከፍተኛ መተራመስ እና ስጋት እንደነገሰ የገለጸው የድረ ገጹ ዜና፣ ሀገራዊ አጀንዳዎችን አንስቶ መወያየት ለከፍተኛ ስቃይ እንደሚዳርግ ገልጿል። በአሁኑ ጊዜ በርካታ ሀገር ወዳድ ወታደራዊ መሀንዲሶች እንደ ቁም እስረኛ ሌት ተቀን በወያኔ ሰላዮች እንደሚጠበቁ ተመልክቷል። በተለይ ባለፈው ሚያዝያ ወር ወያኔ "መፈንቅለ መንግስት ሊሞከርብኝ ነበር" ብሎ በርካታ መኮንኖችን እና ሰላማዊ ዜጎችን በግፍ ካሰረ በኋላ በወታደራዊ መሀንዲሶችና የህወሀት አባላት ባልሆኑ ተራ ወታደሮች ላይ ሳይቀር የሚደረሰው ጫና በእጅጉ ተባብሶ መቀጠሉ ታውቋል፡፤ በዘራቸው እና ለመለስ ዜናዊ ያላቸው ታማኝነት እንደ ችሎታ እና ጀብዱ ተቆጥሮላቸው በመከላከያ ውስጥ ያለውን የጄኔራልነት እና የኮሎኔልነትነት ማእረግ የደረቱት የወያኔ ደናቁርት፣ ከመከላከያ ኢንጂነርግ ኮሌጅ ተመርቀው በሚወጡት ወጣት ባለሙያዎች ላይ ከፍተኛ ጥላቻና ቅናት እንዳላቸው ይታወቃል።

ኮምፒተር እና የተወሳሰቡ መሳሪዎችን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሲመጡ የመለስ ጄኔራሎች ወጣት ወታደራዊ መሀንዲሶቹን የሙጢኝ ብለው እንደሚያስቸግሩ ያገኘነው መረጃ የሚያመለክት ሲሆን መለስ በዘር እና በታማኝነት ከሾማቸው ከፍተኛ መኮንኖች ውስጥ አንድ እንኳን የሲሙሌሽን ሲስተም የሚውያቅ እንደሌለ ተዘግቧል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## መለስ ዜናዊ፣ በኢትዮጵአ ውስጥ ለሚታየው ተደጋጋሚ የመብራት መቋረጥ የሰጠው ምክንያት ሃላፊነት የጎደለው ነው

በደረቅ ውሸቱ የሚታወቀው ዘረኛው መለስ ዜናዊ፣ የአለም ባንክ የጄነሪተር መግዣ ገንዘብ ቢያበድረን ኖሮ የመብራት መጥፋት ችግር ባልተከሰተ ነበር ማለቱን ተከትሎ የተለያዩ ነቀፋ አስተያየቶች በመሰንዘር ላይ ናቸው። አምባገነኑና ዘረኛው መለስ ዜናዊ እንደለመደው የራሱን የአስተዳደር ችግር በሌሎች ላይ በማላከክ ከተጠያቂነት ለማሸሽ የሰጠው ምክንያት የመለስ ዜናዊን ባህሪ ከማሳየት ውጭ ሌላ ጥቅም እንደሌለው አስተያየት ሰጪዎች ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ የአለም ባንክ ተወካይ ሚ/ር ኬንቹ ኮሀሺ "መብራት የሚጠፋው የአለም ባንክ የጄነረተር መግዣ ስላልሰጠ ነው" በሚል የቀረበው አስተያየት "ባዶ ውሸት ነው" ካሉ በሁዋላ አክለው ሲናገሩ "እኛ ገንዘብ አልከለከልናቸውም፣ ነገር ግን ገንዘብ አጠያየቃችሁና አቃ አገዛዛችሁ ግልጽነት ይኑረው ብለን ጠይቀናቸዋል። ገነዘብ የከለከልናቸው አሰራራቸው ግልጽነት የጎደለወውና የአለም ባንክን መስፈርት ማሟላት ስላልቻሉ ነው" በማለት የመለስ ዜናዊን ቅጥፈት አጋልጠዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## *የመለስ ቡድን ዓይን ያወጣ ዝርፊያ በእንግሊዝ ምክር ቤት አባላት ተተቸ*

"በሙስና ዝቅጠት ውድድር ቢደረግ፤ የቃሉን አዲስ ፍች ያገኙልን የኢትዮጵያ መንግስት መሪዎች አሸናፊ ሆነው የወርቅ ሜዳሊያ ባጠለቁ ነበር"ሲሉ የእንግሊዝ ምክር ቤት አባል የተከበሩ ጀምስ ብሩስ ተናገሩ።

ጀምስ ብሩስ ይህን ያሉት በእንግሊዝ የሚኖሩ ከ300 በላይ ኢትዮጵያውያን ባለፈው ሰኔ 9 ቀን የመለስ ዘረኛና አሸባሪ ቡድን በኢትዮጵያውያን ላይ እየፈፀመ ያለውን በዘር ላይ ያነጣጠረ ጭፍጨፋ፣ ለከት ያጣ የሰብአዊ መብት ጥሰት እና በአገሪቷ ላይ እያካሔደ ያለውን መረን የለቀቀ የቡድን ዝርፊያ ለብሪትሽ የተመራጮች ምክር ቤት አባላት ባሰሙበት ወቅት ነው።

ከስብሰባው አስተባባሪዎች መካከል አቶ ወንድሙ መኮንን የእለቱን ክንውን አስመልክተው በድረ-ገፆች ይፋ ባደረጉት ፅሁፋቸው እንደገለፁት፤ "ሀውስ ኦፍ ኮመንስ "ተብሎ በሚጠራው በዚሁ የተመራጮች ምክር ቤት-የተደረገውን ስብሰባ የከፈቱት የእለቱ የክብር እንግዳ የሆኑት የሁሉም ምክር ቤቶች ሊቀመንበር የተከበሩ ዴቪድ አንደርሰን ሲሆኑ ኢትዮጵያውያኑ ያደረጉትን ወደ ሶስት ሰዓታት የወሰደ ገለፃ ፤ የብሪትሽ የፓርላማ አባላትን ጨምሮ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ተወካዮች፣ የትብብር ከሶስተኛው ዓለም ጋር አባላትና ታዋቂ የሚዲያ ሰዎች ተከታትለውታል።

እንደ አቶ ወንድሙ ዝርዝር ሀቅ፤ አሸባሪው የመለስ ቡድን እየፈፀመ ያለውን ግፍ አስመልክቶ በኢትዮጵያውያኑ የተደረገው ገለፃ፤ የብዙዎቹን ዐይን የከፈተና በርካቶቹን "ጉድ" ያሰኘ ነበር።

ከስብሰባው ተሳታፊዎች መብዛት ባሻገር የመለስ ነፍሰ-ገዳይ ቡድን ሆነ ብሎ የፈፀማቸው የዘር ማጥፋት ወንጀሎች እንዲሁም አገዛዙ በሙስና ንቅዘት የደረሰበት አሳፋሪ ደረጃ በፕሮጀክተር ታግዞ በምስል መቅረብ ስለነበረበት ስብሰባው በታላቁ የኮሚቴ ስብሰባ አዳራሽ መካሄዱን የገለፁት አቶ ወንድሙ፤ታዋቂዋ የጋርዲያን ጋዜጣ ዘጋቢ ሳውንድራ ሳተርሊም **"ተሞክሮና የ አሁኑ የሚዲያ ሽፋን በኢትዮጵያ"** በሚል ርዕስ ፅሁፍ ማቅረቧን አመልክተዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ግንቦት 7 በካናዳ ቶሮንቶና ካልጋሪ ከሚኖሩ ኢትየጵያውያን ግር የተሳካ ውይይት አደረገ

አገር ገዳዩንና አሸባሪውን የመለስ አገዛዝ በሚችሉት አቅም ለመታገል መወሰናቸውን በካናዳ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ገለጹ። ኢትዮጵያውያኑ አቋማቸውን የገለጹት የግንቦት 7 ንቅናቄ ያለፉት ቅዳሜና እሁድ በካልጋሪና በቶሮንቶ ከተሞች በጠራው ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ሲሆን፣ ስለ ንቅናቄው ሁለገብ ትግል ከሊቀመንበሩ ከዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ጋር ሰፊ ውይይትና ምክክር ማድረጋቸውም ታውቆአል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

# ርእሰ አንቀጽ



## በእርዳታ ሱስ የሰከረዉን ወያኔ ማስወገድ የዘላቂ ልማት ቀዳሚ አጀንዳ ነው

በስብዓት ነጋ አስቂኝ ዘበዘብ መነሻነት «ኤፈርት-መር ካፒታሊዝም» የተሰኘው የወያኔ ኢኮኖሚ መሠረቱ ሸቀጦችን ማምረት ወይም አገልግሎቶችን ማቅረብ ሳይሆን ከለጋሽ አገሮች የሚገኝ እርዳታን መምጠጥ ነው፡፡ የእርዳታ ፍሰት የወያኔ የሕይወት እስትንፋስ ነው፡፡ ስለሆነም በችግርኛው ስም የሚመጣው እርዳታ ወደ ወያኔ ቋቶች ያለማቋረጥ መፍሰሱን ማረጋገጥ የሹመኖቹ የሙሉ ጊዜ ሥራ ነው፡፡ ወያኔ ምን ያህል በእርዳታ ሱስ የሰከረ ስለመሆኑ በያዝነው ሰኔ ወር ብቻ እንኳን ካስተዋልናቸው ክስተቶች ውስጥ ሶስቱን ብቻ ለአብነት እናነሳለን፡፡

1. ሰኔ 9 ቀን 2001 ዓ.ም በአዲስ አበባ በተደረገው የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም የዳሬክተሮች ስብሰባ መለስ ዜናዊ ተገኝቶ ባደረገው ንግግር የበለፀጉ አገሮች የልማት እርዳታ ሲሰጡ የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ መሻሻልን መጠየቃቸው እና የሚሰጡትም ገንዘብ ከፕሮጀክቶች ጋር መያያዛቸው በእጅጉ አምርሮ ተቃወመ፡፡ እነዚህ «አሳሪ ቅድመ-ሁኔታዎች ናቸው» በማለትም ተከራከረ፡፡ ጉዳዩን ለማክበድም «የበለፀጉ አገሮች በእርዳታ ሰበብ የኢኮኖሚ ሉዓላዊነታችንን እየተጋፉ ነው» አለ፡፡ ከዚህ ሁሉ የምሬት ንግግር በኋላ ግን አገሮቹ ያለ አንዳች ቅድመ-ሁኔታ የሚሰጡት እርዳታ መጨመር እንዳለባቸው ተማፀነ፡፡ ከሶስት ቀናት በኋላ ሰኔ 12 ቀን ባደረገው ቃለ-መጠይቅ ደግሞ ለኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት ምክንያቱ የዓለም ባንክና ለጋሽ አገሮች ናቸው እኛ የሰጠናቸውን የእድገት አሃዝ አምነው ብድር ስላልሰጡን ነው ይኽ ችግር ሊከሰት የቻለው፤ ስለሆነም ጥፋቱ የነሱ ነው አለ፡፡ የመለስ እርስ በርሱ የተጣላ ንግግር ትርጉሙ ቢያንስ ለኛ ለኢትዮጵያዊያን ግልጽ ነው - ለጋሽ አገሮችን «ገንዘባችሁን በርከት አድርጋችሁ ስጡን እንጂ በሰጣችሁን ገንዘብ ምን እንደምናደርግበት አትጠይቁን» እያላቸው ነው፡፡ የመለስን የሰዓታት ንግግር «ገንዘቡን አምጡ፤ ቁጥጥሩን ግን እርሱት» በሚል መፈክር ማሳጠር ይቻላል፡፡

2. በያዝነው ሰኔ ውስጥ ከዘጠኝ ሚሊዮን በላይ ወገኖቻችን አስቸካይ እርዳታ ይፈልጋሉ፡፡ በመላው ዓለም ላይ በደረሰው የኢኮኖሚ ቀውስ ሳቢያ ለኢትዮጵያ የሚሆን የምግብ እርዳታ ማገኘት ቀድሞ ከነበረው ይበልጥ ፈተና ሆኗል፡፡ በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የዓለም የምግብ ድርጅት በከፍተኛ ጥረት አሰባስቦ ጂቡቲ ወደብ ያደረሰውን እርዳታ ወደ መሃል አገር ማድረሻ አጥቶ ተቸግሯል፡፡ የአጋጣሚ ነገር ሆነና የኤፈርቱ ትራንስ ኢትዮጵያ የጭነት ማመላለሻ አገልግሎት ቀድሞ የወሰደው ማዳበሪያን የማድረስ ኮንትራት አለበት፡፡ ሌሎች ድርጅቶች ወይም የግል የጭነት አገልግሎቶች እርዳታውን አድርሰው የኤፈርት ገቢ ከሚጎዳ ድሃው ተርቦ ቢሞት ይመርጣሉና ሰበብ እፈጠሩ እስካሁን የምግብ ማጓጓዙ ሥራ እንደተጓተተ ነው፡፡ የዓለም የምግብ ድርጅት ከሱዳን የትራስፓርት ማጓጓዣዎች የመጠቀምን አማራጭ መፍትሄ ቢያቀርብም መንግሥት ተብዮው ኤፈርት እንዳይጎዳበት ሃሳቡን ተቃወመ፡፡ የእርዳታ ማድረስ ሥራ መስተጓጎሉና የረሃቡ መጠንም እየከፋ መሆኑን ያሳሰበው የድርጅቱ የአዲስ አበባ ቢሮ ስለተሰማው ቅሬታ መግለጫ በመስጠቱ የወያኔ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስማችን አለአግባብ ጠፍቷልና የዓለም የምግብ ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት የአዲስ አበባ ቢሮን መግለጫ ያስተባብል፤ ይቅርታም ይጠይቀን አለበዚያ ግን የእርዳታው እህል ከጂቡቲ አይንቀሳቀስም አለ፡፡ ድርጅቱ ዘጠኝ ሚሊዮን ረሃብተኞች በመያዣነት መያዛቸውን እግምት ውስጥ በማስገባት የይስሙላም ቢሆን የወያኔን መንግሥት ይቅርታ ጠየቀ፡፡ «አይጋ» የተባለው የወያኔ ድረ-ገጽ ደብዳቤው ለጥፎ በደስታ እያቅራራ ነው፡፡

3. በዚሁ ሰኔ ወር የ2002 ዓ.ም የፌደራል በጀት ፀድቋል፡፡ ይህ በጀት አንድ ሶስተኛ ያህሉን ገቢ ተስፋ ያደረገው በእርዳታና ብድር ነው፡፡ ይህ ብድርና እርዳታን ተማምኖ የተሰላው በጀት ግን ለጦር ሠራዊቱና ለስለላ የሚያወጣው ወጪ ያው እንደተለመደው ከፍተኛ ነው፡፡ የታሰበው እርዳታና ብድር ቢገኝ እንኳን የታቀደው ወጪ ከገቢው በአስር ቢሊዮን ብር ይበልጣል፡፡

እነዚህ በላይ የተዘረዘሩት ሶስት የሰኔ ወር ክስተቶች የሚያስገነዝቡን ወያኔ እና ኩባንያዎቻቸው እየከበሩ ያሉት በድሃው መራብ በመሆኑ የወያኔ አመራር ችጋርን ከኢትዮጵያ የማጥፋት ፍላጎትም ችሎታም ሊኖራቸው እንደማይችል፤ ወያኔ ረሃብን የፖለቲካ መጠቀሚያ እያደረገ መሆኑን እና የእርዳታው ፍሰት አደጋ ከገጠመው በሚቀጥለው በጀት ዓመት የወያኔ መንግሥት ኢኮኖሚ ተንኮታኮቶ ፈጽሞ ሊቆም የሚችል መሆኑን ነው፡፡

ዋነኛ የገቢ ምንጮቹ በመሆናቸው ወያኔ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ ኢትዮጵያ ከችጋርና ረሃብ መላቀቅ አትችልም፡፡ ይህ በእርዳታ ሱስ ናላው የዞረበትን ወያኔን ማስወገድ ችጋርን ከኢትዮጵ ምድር ለማጥፋት ለሚደረገው ትግል የመጀመሪያው ወሳኝ ምዕራፍ ነው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ አገር ወዳድ ወያኔን ማስወድ የድህነት ቅነሳ ትግሉ አቢይ ምእራፍ መሆኑን ተገንዝቦ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የወያኔን የገቢ ምንጮች በማድረቅ ራሱ፣ ቤተሰቡንና አገሩን ያድን እንላለን፡፡

### *የመለስ ቡድን ዓይን ያወጣ ዝርፊያ በእንግሊዝ ምክር ቤት አባላት ተተቸ*

*(ከገጽ 1 የዞረ)*

ከሶስት ሰዐታት ትኩረት ሳቢ ገለፃና ውይይት በሁዋላ የዕለቱን ስብሰባ የዘጉት የተከበሩ ጀምስ ብሩስ- ስለ ኢትዮጵያ መሪዎች አሳፋሪ የሙስና ቅሌት ያደረጉት ንግግር የብዙዎቹን ትኩረት መሳቡ ታውቋል። "በሙስና ዝቅጠት ውድድር ቢደረግ፤ የቃሉን አዲስ ፍች ያገኙልን የኢትዮጵያ መንግስት መሪዎች አሸናፊ ሆነው የወርቅ ሜዳሊያ ባጠለቁ ነበር" ሲሉ አስረድተዋል የተከበሩ ጀምስ ብሩስ።

እንደ አቶ ወንድሙ ፅሁፍ፤ ጀምስ ብሩስ ይህን ሲሉ፤ የስብሰባው ተሳታፊዎች በሳቅ አጅበዋቸዋል። ጀምስ ብሩስ ከዚህም ባሻገር በመጪው ጊዜ በጉዳዩ ዙሪያ ከኢትዮጵያውያኑ ጋር በተጠናከረ መንገድ የመረጃ ማሰባሰብ ስራ ለመስራት ቃል ገብተዋል። 'ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ...." ይላሉ አቶ ወንድሙ ' **ቀደዱ እንጂ አልዋሹም'** በሚል ርዕስ ባቀረቡት ፅሁፋቸው '.......ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ - ልማደኛውና በእንግሊዝ የኢትዮጵያ አምባሳደር ተብየው ብርሀኑ ከበደ እንደሳቸው አገላለጥ ጨለማው ከበደ ፣ የተጠቀሰው ዓይነት ስብሰባ እንዳልተደረገ በመናገር በአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ የውሸት ስልቻቸውን ሞልተው ተረተሩት"

አምባሳደር ብርሀኑ ከበደ ጉዳዩን አስመልክቶ ለቪ.ኦ.ኤ በሰጠው አጭር ቃለምልልስ ስድስት የሚሆኑ ሀቆችን ሸምጥጦ እንደካደ ወይም ስድስት ትላልቅ ውሸቶችን ያለምንም ማፈርና ይሉኝታ እንደዋሸ በመረጃ አስደግፈው በዝርዝር ያስረዱት አቶ ወንድሙ፤ አምባሳደር ተብየው ምርጫ 97ትንም ተከትሎ ተመሣይ ውሸቶችን ብሚዲያ ሊያራግብ እንደነበር አስታዎሰዋል።

ሆኖም ያን ጊዜም ልክ እንደ አሁኑ ከቪ.ኦ.ኤ እና ከጀርመን ጋዜጠኞች አፍጥጠው ለመጡበት የሀቅ ጥያቄዎች የሚለው ጠፍቶት መደናገሩንና የብዙዎች መሳቂያ መሆኑን ያስታወሱት አቶ ወንድሙ፤ "ተላላኪው አምባሳደር ካለፈው ትምህርት ወስደው ሳይገድሉ ጎፈሬ ሳያረጋግጡ ወሬ አይደግማቸውም ብለን ተስፋ አድርገን ነበር፤ ዳሩ ምን ያደርጋል? አመል አይለቅምና ደገሙት"ብለዋል።



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ለነፃነት በምናደርገው ትግል የሲቪል ማኅበራት ሚና

በለንደን ስብሰባ የቀረበ ታደሰ ብሩ (ዶ/ር) (ካለፈው የቀጠለ)

## ምን መደረግ አለበት?

በሌላ በኩል ደግሞ የሲቪክ ማኅበራትን አቅም በመረዳት ረገድ ወያኔ የበለጠን ይመስለኛል፡፡ በዚህም ምክንያት ሲቪል ማኅበራትን ለማጥፋት የተጠና እርምጃ እየወሰደ ነው፡፡ እኛ ግን የሲቪል ማኅበራትን አቅም በደንብ የተረዳን አይመስለኝም። ከታሪክ የምንማረዉ ግን ታላላቅ የነፃነት ትግሎች የተደረጉት በሲቪል እንቅስቃሴዎች ነው፡፡ በብዙ አገሮች የባሮች፣ የጥቁሮች፣ የሴቶች፣ የሠራተኞች ... አሁን አሁን ደግሞ የህፃናትን፣ የአካል ጉዳተኞችን፣ የአናሳ ዘውጌ ማኅበረሰቦችን .. መብቶች ለማስከበር ሲቪል ማኅበራት ከፓለቲካ ፓርቲዎች የተሻለ ውጤት አምጥተዋል፡፡ በአንዳንድ አገሮች ሲቪል እንቅስቃሴዎች የፓለቲካ ሥርዓት ለውጥ አምጥተዋል፡፡ ምሥራቅ አውሮፓ በተለይም ደግሞ ፓላንድና ቼክ ሪፑብሊክ የቅርብ ጊዜ ምሳሌዎች ናቸዉ፡፡ አፍሪካም ውስጥ ጋና እና ኬኒያ በአርዓያነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

የኛ ሲቪል ማኅበራት የሚከተሉት ዋና ዋና ችግሮች ያሉባቸው ይመስለኛል፡-

1. ከፓለቲካ ገለልተኛ ነን ብለው የሚያታልሉ መሆናቸው
2. ጠባብ አጀንዳ ይዘው የሚንቀሳቀሱ መሆኑ
3. የተበጣጠሱ፣ ትናንሽ አካላት መሆናቸው
4. እንቅስቃሴዓቸው የግብር-ይውጣህ ዓይነት መሆኑ

ወያኔ ሲቪል ማኅበራት በፓለቲካ መግባት የለባቸውም ማለቱ እጅግም የሚገርም አይደለም፡፡ ሁሉም ሰው ፖለቲካን ቢጠላ ወያኔ ደስታው ነው፡፡ የሚገርመው ግን የኛዎቹ ሲቪል ማኅበራት ራሳቸው ይህንን መቀበላቸው ነው፡፡ ፓለቲካን ሳይነኩ ለመብት መታገል የሚሆን ነገር አይደለም፡፡

ከዚሁ ትንሽ ለየት የሚለው ነጥብ ደግሞ ዝነኛዉ «የገለልተኝነት» መርህ ነው፡፡ የአገራችን ሲቪል ማኅበራት በደፈናው «ገለልተኛ» ነን ማለት ይቀናቸዋል፡፡ ሲያብራሩትም «አገራችንን እንወዳለን፤ ለአገር የሚጠቅም ነገር እንሠራለን ግን ለይተን የምንደግፈው ወይም የምንቃወመው ፓርቲ የለም» ይላሉ፡፡ ከፓርቲ ፓለቲካ ገለልተኛ መሆን አንድ ነገር ነው፡፡ በነፃነት ጉዳይ ገለልተኛ መሆን ግን አይቻልም፡፡ ወይ ለነፃነቱ ከሚታገለው ባርያ ጎን፤ አልያም ከባርያ አሳዳሪው ጋር መቆም ግድ ነው፡፡ ገለልተኛነት የባርያ አሳዳሪውን የሚጠቅም ከሆነ ሲቪል ማኅበራት በግልፅ ከባርያው ጎን መቆም ይኖርባቸዋል፡፡ እንደታዘብኩት የገለልተኝነት መርህ ኢትዮጵያዊያን ሲቪል ማኅበራት ለነፃነት ትግል ሊያበረክቱት ይችሉ የነበረውን አስተዋጽዖ በእጅጉ የቀነሰባቸዉ ይመስለኛል፡፡ አሁን የተያያዝነው ትግል ለአርነት፣ ለነፃነት የምናደርገው ትግል ነው፡፡ እንደ ሰው ፍጡራን ሊኖሩን የሚገቡ መብቶቻችንን በግፍ በመነጠቃችን የምናደርገው ትግል ነው፡፡ ማንኛውም ሲቪል ማኅበር/ማኅበረሰብ በዚህ ጉዳይ ገለልተኛ መሆን አይገባውም፡፡

በተለይ እንዳሁኑ ትግሉ በሚመርበት ወቅት ሲቪል ማኅበራት አቋማቸዉን በግልፅ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ወይ ለነፃነቱ ከሚታገለው የኢትዮጵያ ሕዝብ አለያም ከጨቋኙ ወያኔ ጋር መወገን ይገባል፡፡ ሶስተኛ መንገድ አለኝ ሲል የሰማነው ማንን ነበር? እሱ ሶስተኛ ብሎ ይጥራው እንጂ ሕዝቡ የሚያውቀው ባንደኛው ተቀጣይነቱ ነው፡፡

በተለይ ሚዲያ ከፓርቲ ፓለቲካ ጋር እጅግ የተያያዘ መሆኑን ከአዉሮፓ ታሪክ መማር ያለብን ይመስለኛል፡፡ የታወቁ የሚዲያ ኩባኒያዎች ለአንዱ ወይም ለሌላኛው ፓርቲ ሲያዳሉ ማየት አዲስ ነገር አይደለም - ድሮም እንደዚሁ ነበር፤ ወደፊትም እንደዚሁ የሚቀጥል ይመስለኛል፡፡ ይህ መልዕክቴ ለኢትዮጵያ ፓልቶክ ሩሞችም ጭምር ይሁንልኝ፡፡ አንዳንዶቹ በሚዛናዊነት ስም ለወያኔ ካድሬዎች ማይክ እየለቀቁ ክፍሉን የወያኔ ሬዲዮ ሲያስመስሉት መታዘብ ያሳዝናል፡፡

እርግጥ ነው የኢትዮጵያ መምህራን፣ የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች፣ የኢትዮጵያ ወጣቶች፣ የኢትዮጵያ ሴቶች፣ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች፣ የኢትዮጵያ ሞስሊሞች ወዘተ ማኅበራት እንደተቋቋሙበት ዓላማ የተለያዩ አጀንዳዎች አሉዋቸው፡፡ ያም ሆኖ ግን ሁሉንም የሚያስተባብራቸው የጋራ አጀንዳዎች በርካታ ናቸው፡፡

በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ለመብት መቆማቸው ሁሉንም የሚያስተባብራቸዉ አጀንዳ ነው፡፡ መብት ከአንዱ ተቀንሶ ለሌላው የሚሰጥ ነገር አይደልም፡፡ እንዲያውም የአንዱ መብት መጓደል፤ የሌላኛውንም መብት መጓደል ያስከትላል፡፡ የመምህራን መብት መጣስ መምህራንን ብቻ ሳይሆን ሁላችንንም የሚሳስበን ጉዳይ መሆን ይኖርበታል፡፡ የጋዜጠኞች፣ የወጣቶች፣ የሴቶች መብቶች መጓደል እንደዚሁ የሁላችንም ጉዳይ ነው፡፡ በሞስሊሞች መበደል ክርስቲያኖች፤ በክርስቲያኖች መበደል ሞስሊሞች ሊያማቸው ይገባል፡፡ የነፃነት፣ የመብት ጥያቄዎች ሁላችንን የሚያስተባብሩን ናቸው፡፡ ሲቪል ማኅበሮቻችን አጀንዳዎቻቸዉን አስፍተው መንቀሳቀስ ይኖባቸዋል፡፡ የተበጣጠሰ ትግል የትም አያደርሰንም፡፡

ሁሉም ሲቪል ማኅበራት የኢትዮጵያዊያን ማኅበር መሆናቸው ሌላው ትልቅ የጋራ አጀንዳ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ህልውና ጉዳይ ላይ በጋራ መቆም ካልቻሉ በሌሎች ጉዳዮች ላይ በጋራ ይቆማሉ ብሎ ማሰብ ዘበት ነው፡፡

እዚህ ላይ ስለ ግንቦት ሰባት፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ጥቂት ልበል፡፡

ብዙዎቻችሁ እንደምታውቁት ግንቦት ሰባት - የትምህርት፣ የጤና፣ የግብርና፣ የኢንዱስትሪ ፓሊሲ የለውም፡፡ አስቀድሞ በተዘጋጀባቸው ፓሊሲዎች መሠረት ኢትዮጵያን ለማስተዳደር የሚፈልግ የፓለቲካ ድርጅት አይደለም፡፡ የግንቦት ሰባት ዓላማ ኢትዮጵያን የመምራት ፍላጎቱም ችሎታው አለን ብለው የሚያምኑ ድርጅቶች ዓላማቸውን ለሕዝብ አሳውቀው እንዲወዳደሩ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ከቀረቡለት ምርጫዎች ውስጥ የፈለገውን መርጦ ለመሾም፤ ሳይስማማው ደግሞ ለመሻር የሚያስችለውን መንገድ ማመቻቸት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ እሁን ሲሆን የግንቦት 7 ዓላማ ግቡን ስለመታ ከዚያ በኋላ የመቆያ ምክንያት የለውም፡፡ ሥልጣን የሚያዝበት አግባብ ፍትሃዊ እንዲሆን ማድረግ እንጂ ሥልጣን መያዝ የግንቦት ሰባት ዓላማ አይደለም፡፡

እና ግንቦት 7 የፓለቲካ ፓርቲ ነው ወይስ የሲቪል ንቅናቄ?

ከፓርቲ ፓለቲካ ገለልተኛ ነኝ የሚል ሲቪል ማኅበረሰብ እንኳን ቢሆን ሲቪል ማኅበረሰብ በኢትዮጵያ እንዲኖር የሚፈልግ እስከሆነ ድረስ ከግንቦት ሰባት ጎን የመቆም የሞራል ግዴታ አለበት፡፡

የተከበራችዉ ወንደሞቼና እህቶቼ እንኳንስ ሲቪል ድርጅት ፓለቲካ አልወድም የሚል ግለሰብ እንኳን ቢሆን ግንቦት ሰባትን የማይደግፍበት ምክንያት የለውም፡፡ የፓርቲ ፓለቲካን ወደድንም ጠላንም፤ በአገራችን የፓለቲካ ሥልጣን ከምርጫ ሣጥን ብቻ እንዲመነጭ የምንፈልግ ከሆነ ከግንቦት ሰባት ጋር የምንጋራዉ ዓላማ አለ ማለት ነው፡፡ እናም በትግሉ አጋዥነት ራሳችንን ብናሰልፍ የፓርቲ ፓለቲካ ወገንተኛ አያደርገንም፡፡

ከአሁን በኋላ ውስን አጀንዳዎችን በያዙ ትናንሽ ሲቪል ማኅበራት ላይ ጊዜዓችንንና ጉልበታችንን ከማጥፋት ኃይላችንን አስተባብረን ለነፃነታችንና ለአገራችን መቆም ይኖርብናል፡፡ በቅርቡ የተጀመረው የኢትጵያዊያን ሲቪክ ማኅበራትን በዓለም-ዓቀፍ ደረጃ የማደራጀት እንቅስቃሴ በጣም የሚደገፍና የሚበረታታ ተስፋ ሰጭ ጅምር ነው፡፡

በመጨረሻም የሲቪል ንቅናቄ የምር መያዝ ያለበት ጉዳይ መሆኑን ማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡ የአንዳንዶች ሲቪል ማኅበራት እንቅስቃሴዎች ተከታታይነት የሌላቸው፣ በእቅድ ያልተደገፉ፣ በግማሽ ልብ የሚደረጉ የትርፍ ጊዜ ተግባራት በመሆናቸው እምብዛም ውጤት የላቸውም፡፡ ይህ መቀየር ይኖርበታል፡፡ እንዲያውም ጉልበታችንን፣ ጊዜዓችንና ገንዘባችንን አቀናጅተን ቅድሚያ ለነፃነታችንና ለአገራችን ብለን በአድነት ከተነሳን ድሉ ቅርብ ነው፡፡

## ማጠቃለያ

ወያኔ ሲቪል ማኅበራትን በማጥፋት አብሮ ለመኖር፤ ተባበሮ ለመሥራትና ተጋግዞ ለማደግ የሚያስችለንን መተማመን በመካከላችን እንዳይኖር - በፍቅር ፈንታ ጥላቻና ጥርጣሬ እንዲንሰራፋ እያደረገ ነው፡፡

ለዚህ የምንሰጠው ምላሽ ደግሞ በተኛጠል ትናንሽ እንቅስቃሴዎች ጊዜና ጉልበታችንን ከማጥፋት ትግላችንን አስተባብረን ፍትህ የሰፈነባት ነፃይቱን ኢትዮጵያ ለመገንባት ቆርጥን እንነሳ

በኅብረት ከተነሳን የወያኔ የአገዛዝ እድሜ አጭር ነው፤ ታጥቀን እንነሳ

አመሰግናለሁ፡፡

## በመከላከያ ሠራዊቱ ውስጥ ያለው የአዛዥነት ቦታዎች በትግራይ

(ከገጽ 1 የዞረ)

በተመሳሳይ በፌዴራልና በክልል ፖሊስ አባላት ዘንድም ዘገባው ከፍተኛ ማጉረምረምና ጥያቄ መፍጠሩ ተመልክቷል።

በተለያዩ ክፍለ ጦሮች ውስጥ ወያኔ በለመደው አባላትን የማሸማቀቂያ የግምገማ ስብሰባ ላይ እስከዛሬ ባልተለመደ ድፍረት " ከ61 ከፍተኛ የመከላከያ ቦታዎች 57ቱ፤ እንዲሁም በአገሪቱ ከሚገኙ 38 ጄኔራሎች 28ቱ ለትግራይ ተወላጆች ብቻ የተሰጠው የሌሎች ብሔረሰብ ተወላጆች የሆንን ለዛ ቅባት የሚመጥን ተፈጥሮና ሙያ ስለሌለን ነውን?" በማለት መጠየቃቸው የተሰማ ሲሆን፤" በብሔር ተዋፅኦና እኩልነት ስም እየተፈጸመ ያለው ዘረኝነት እስከዛሬ ከራሱ ከሰራዊቱ ተደብቆ የቆየው በሰራዊቱ ውስጥ ሆን ተብሎ በተዘረጋው ጥብቅ የስለላ ሰንሰለት ምክንያት ሰው አርስ በርሱ ስለማይተማመንና ስለማይነጋገር እንደሆነ ጭምር መነሳቱ ተገልጾአል ። የሰራዊቱ አባላት ለመጀመሪያ ጊዜ እያሳዩት ባለው በዚህ ድፍረት የተነሳ የወያኔ አዛዦችና የበላይ አለቆቻቸው እነመለስ ዜናዊ ከፍተኛ የሆነ ድንጋጤና መረበሽ ውስጥም እንደተዘፈቁ ተያይዞ የደሰን መረጃ አመልክቶአል።

"ዘመኑ በተሻሻለበት በአሁኑ ወቅት ይህን እያዩና እየሰሙ በዝምታና በፍርሀት መቀመጥ ውርደትና ባርነትን በፈቃድ ከመቀበል ባሻገር በቁም እንደመሞት ይቆጠራል" በማለት ለግንቦት ሰባት ዘጋቢ አስተያዬታቸውን የሰጡት አንድ የፌዴራል ፖሊስ አፍሰር ፣ "ፊጣና አልሙትም፤ ዘበርጋና ኡጅሉም፤ መሀመድና አለሚቱም ለአመራርነትም ሆነ ለጄኔራልነት ብቁ መሆናችንን የምናሳይበት ቀን ሩቅ አይደለም" ብለዋል።

በዚህ አጋጣሚ፣ ግንቦት 21 ቀን በግንቦት ሰባት ድምፅ በተላለፈው ዘገባ "የ35ኛው ክፍለ-ጦር አዛዥ ኮሎኔል ምስጋናው ዓለሙ- ከአገው ብሔረሰብ" ተብሎ የተዘገበው በስህተት ስለሆነ "የ35 ኛው ክፍለ-ጦር አዛዥ ኮሎኔል ይበራ ዘሪሁን -ከትግራይ ብሔረሰብ" ተብሎ እንዲስተካከል ከይቅርታ ጋር እንጠይቃለን።

ይህም በመከላከያ ውስጥ ካሉ 61 ቁልፍ ቦታዎች 57 እንደነበር ተደርጎ የተዘገበውን የትግራይ ተወላጆች ቁጥር ወደ 58 ከፍ የሚያደርገው ሲሆን፤ ቀሪዎቹ ሦስት ቦታዎች ሁለቱ በአማራ አንዱ በአገው ተወላጆች የተያዘ እንደሆነና ባለፈው ዘገባችን እንደገለጽነው በህዝብ ብዛት የመጀመሪያው መሆኑ የሚነገርለት የኦሮሞ ህዝብን ጨምሮ ለሎች ብሄረሰባ የአዛዥነት ስልጣን ተቋዳሽ እንዳይሆኑ የተፈረደባቸው መሆኑ ታውቆአል። ከወያኔ መስራች አንዱ የሆነው ስብሃት ነጋ በቅርቡ በውጭ አገር ላለ አንድ የወያኔ ሬዲዮ በሰጠው ቃለ መጠይቅ የትግራይ በላይነት በሰራዊቱ ውስጥ መስፈኑን አምኖ በሂደት መስተካከል እንደሚኖርበት ተናግሮ አንደነበር መዘገባችን ይታወሳል።

እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ብዙዎች "ወያኔ በእርግጥም እንደሚያወራው ለብሔረስብ መብትና እኩልነት የቆመ መስሏቸው 'ከብሔር መብትና ከግለሰቦች መብት የትኛው መቅደም አለበት?' የሚል አካዳሚያዊና ፖለቲካዊ ክርክር ውስጥ ገብተው ከወያኔ ጋር መሟገታቸውን ያስታወሱት አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር የፓርላማ አባል በበኩላቸው፣ "የወያኔ የብሄረሰብ መብት ጠባቂነት መፈክር ፌዝ ለመሆኑ ይህ የሹመት ዘገባ በጣም ፍንትው ያለ ማሳያ ይሆናል ብየ አምናለሁ" በማለት ላነጋገራቸው የግንቦት 7 ዘጋቢ ተናግረዋል።

## መለስ ዜናዊ፣ በኢትዮጵአ ውስጥ ለሚታየው ተደጋጋሚ የመብራት መቋረጥ የሰጠው ....

(ከገጽ 1 የዞረ)

የባንኩ ሀላፊንግግር የመለስ ዜናዊን ቅጥፈት የሚያጋልጥ ብቻ ሳይሆን፣ የዌአኔው አስተዳደር በሙስና የተዘፈቀ መሆኑንና የአለም ባንክም በዚህ ደስተኛ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው የሚሉ አስተያየቶችም ተሰጥተዋል።

መለስ ዜናዊ ጄኔረተሩ በህውሀት ንብረት በሆነው ኢፈርት ኩባንያ ስር ባለ አንድ አስመጭና ላኪ ድርጅት በኩል እንዲቀርብ ትእዛዝ ማስተላለፉ የታወቀ ቢሆንም፣ የአለም ባንክ ግን ይህንን ግልጽነት የጎደለውና አገርን የሚጎዳ አሰራር በመቃወም ገንዘብ መከልከሉን የደረሱን መረጃዎች አመልክተዋል።

መለስ ዜናዊ የአገሩቱን ኢኮኖሚ አሳድጌያለሁ እያለ የኢትዮጵያን ህዝብ በውሸት ሲያደነቁር መክረሙን የሚያስታውሱት አስተያየት ሰጪዎች፣ አሁን የአንድ ጄነሬተር መግዣ ገንዘብ አጥቻለሁና አበድሩኝ ማለቱ ሲወራለት የነበረውን እድገት ሁሉ አስቂኝ ያደርገዋል ብለዋል።

ሌሎች ደግሞ ቀጣፊው መለስ ዜናዊ የአለም ባንክ ገንዘብ እንደከለከለው ሲያውቅ ከአላሙዲን ሀብት የበለጠ ሀብት እንዳለው በአቦይ ስብሀት ከተነገረለት ኢፈርት ኩባንያ ገንዘብ በመበደር ጄነሬተር መግዛት ለምን አልቻለም የሚል ጥያቄ አንስተው፣ አሁን ችግሩ አፍጥጦ ሲመጣ የእናቴ መቀነት አደናቀፈኝ ማለት ተቀባይነት አይኖረውም ሲሉ ተናግረዋል።

አንዳንዶች ደግሞ ግልገል ጊቤ ቁጥር 2 በቅርብ ጊዜ ስራ ሲጀምር የመብራት እጥረቱ መቀረፍ ብቻ ሳይሆን ወደ ውጭ አገርም የመብራት ሀይል ይላካል እየተባለ ባለበት ሰአት ለአጭር ጊዜ ተብሎ ገንዘብ መበደርና ጄነረተር መግዝት አብሮ የሚሄዱ ነገሮች አይደሉም ካሉ በሁዋላ የወያኔ አስተዳደር ለፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ እያለ የሚዋሸው እራሱን እያጋለተው ነው ብለዋል፣ ሌሎች ደግሞ እርባና ለሌለውና ሽንፈት ለተከናነበበት የሶማሌ ጦርነት ያወጣው ገንዘብ በብዙ ሺ የሚቆጠር ጄነረተሮችን ያስገዛ ነበር ሲሉ ተናግረው፣ የመብራት መቋረጡ በመጨረሻዎቹ የመንግስቱ አገዛዝ ዘምን ከነበረውም በባሰ ሁኔታ መገኘቱ፣ አገዛዙ ኢትዮፕአን ለማስተዳደር እንደተሳነው ያሳያል ብለዋል። የኢትዮጵያ ህዝብም በረሀብ ና በመብራት እጦት የሚያሰቃየውን ወያኔን በቃህ ሊለው እንደሚገባ አስተያየት የሰጡን ሰዎች ተናግረዋል።

በተያያዘ ዜናም ስልጣኔን እለቃለሁ ሲል የነበረው መለስ ዜናዊ፣ ድርጅቴ ካመነብኝ ለሚቀጥሉት አምስት አመታት በስልጣን ላይ እቅአለሁ ብሎ መናገሩ ድሮውንም ህዝቡን በማደናገር በስልታን ላይ ለመቆየት የተጠቀመበት ዘዴ እንደነበር አስተያየት የጠየቅናቸው የህግ ባለሙያ ተናግረዋል።

## በመፈራረስ ላይ ያለው የዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ሰራዊት አባለት ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በመሸሽ ላይ

(ከገጽ 1 የዞረ)

ይህ በእንዲህ እንዳለ ባለፈው የካቲት ኢንጅነር አንሙት ደመቀ፣ ኢንጂነር ተስፋዬ እና ኢንጅነር ንጉሴ ግርማ ቱሉ የተባሉ የመከላከያ መሀንዲሶች ወያኔን መክዳታቸውን መዘገባችን ይታወቃል።ወያኔ በለመደው ሃላ ቀር እና ያፈጀ አሰራር መሰረት የከዱትን ኢንጅነሮች ቤተሰብ ማሰቃየቱን እና ያሉበትን እንዲጠቁሙ ማስገደዱም ታውቋል።በከፍተኛ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ያለው ወያኔ የሚከዳው የሰራዊት ቁጥር እና ሲቪል ባለስልጣን በመበራከቱ የከዳውን ሰው ቤተሰብ ማሰቃየት መጀመሩ እና አገዛዙን የከዳ ማንኛውም ሰው ንብረቱ እንዲወረስ እና በባንክ ያለው ተቀማጭ እንዳይነቀሳቀስ የሚያዝ ህግ ማውጣቱ ይታወሳል።

## ግንቦት 7 በካናዳ ቶሮንቶና ካልጋሪ ከሚኖሩ ኢትየጵያውያን ግር የተሳካ ውይይት አደረገ

(ከገጽ 1 የዞረ)

ባለፈው የግንቦት ወር በአውሮጳ የተለያዩ ከተሞች በመዘዋወር ለተለያዩ የአውሮፓ መንግሥታት ተወካዮችና በየአገሩ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ስለ አገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ገለጻና ማብራሪያ ሰጥተው የተመለሱት የንቅናቄው ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ በሁለቱም የካናዳ ከተሞች ለተሰበሰበው ህዝብ አገራችን አሁን ያለችበትን ሁኔታና የተጋረጠባትን አደጋ በዝርዝር ማስረዳታቸውም ተገልጾአል። ተያይዞ በደረሰን ዜና በሁለቱ ከተሞች ከሚኖሩ በርካታ ነዋሪዎች በተጨማሪ ቁጥራቸው ቀላል ያልሆነ ሰዎች ከተለያየ የአገሪቱ ክፍል ረጅም ርቀት ተጉዞ በስብሰባው ላይ እንደተገኙና ፤ንቅናቄው ለሚያከናውናቸው የሁለ-ገብ ትግል ማስኬጃ መጠኑ ብዙ የሆነ ገንዘብ ማዋጣታቸውም ታውቆአል።

በአገራችን ላይ የተንሰራፋውን ዘረኛ የወያኔን አገዛዝ በተባበረ የህዝብ ትግል መንግሎ በመጣል በምትኩ ለሁሉም እኩል የሆነች ፡ የዘጎች ሁሉ መብትና ነጻነት ያለገደብ የተከበረባት በኢኮኖሚ የበለጸገች አገር ለመመስረት ግንቦት 7 የጀመረውን ሁለገብ ትግል ፍትህና ነጻነት የጠማው ወገን የመርዳት ሃላፊነት እንዳለበት ለማስገንዘብ በሚቀጥለው የሃምሌ ወር በተለያዩ የአሜሪካ ከተሞች ተመሳሳይ ስብሰባዎችን የማድረግ እንቅስቃሴ እንደሚቀጥል የንቅናቄው ህዝብ ግንኙነት ለዝግጅት ክፍላችን በላከው ማስታወሻ ገልጾአል።

ወያኔ ሲቪል ማኅበራትን በማጥፋት አብሮ ለመኖር፤ ተባበሮ ለመሥራትና ተጋግዞ ለማደግ የሚያስችለንን መተማመን በመካከላችን እንዳይኖር - በፍቅር ፈንታ ጥላቻና ጥርጣሬ እንዲንሰራፋ እያደረገ ነው።

ለዚህ የምንሰጠው ምላሽ ደግሞ በተኛጠል ትናንሽ እንቅስቃሴዎች ጊዜና ጉልበታችንን ከማጥፋት ትግላችንን አስተባብረን ፍትህ የሰፈነባት ነፃይቱን ኢትዮጵያ ለመገንባት ቆርጥን እንነሳ ዶ/ር ታደሰ ብሩ

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org